GLOBAL RESEARCH NETWORK ON PARLIAMENTS AND PEOPLE

የሕፃናት ጋብቻን የተመለከቱ ህጎች፣ ስምምነቶች፣ ቻርተሮችና ስልታዊ ማዕቀፎች በአማራ ክልል ለሚገኙ ተቋማት የተዘጋጀ

<u>አዘጋጆች :</u>

ዶ/ር ሰብለወንጌል አይናለም፤

ዶ/ር ሰዉመሆን ደምሴ፤

ዶ/ር ዘንያ ዮን፤

GLOBAL RESEARCH NETWORK ON PARLIAMENTS AND PEOPLE

This project is funded by PARLIAMENTS AND PEOPLE PROGRAMME

በ2010 ዓ.ም በስማዳ ወረዳ፤ አማራ ክልል አግብተው፤ ነፍሰጡር ሆነው የተገኙ ህጻናት

GLOBAL RESEARCH NETWORK ON PARLIAMENTS AND PEOPLE

ማውጫ

1. መግቢያ.....2
2. የህጻናት ጋብቻን እና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የተመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች እና ስትራቴጅዎች.....3
3. የህጻናት ጋብቻን ለመከላከል/ለማስቆም የሚሰሩ ተቋማዊ አደረጃጀቶች.....8

መግቢያ

በኢትዮጵያ በመልካም ተሞክሮነት ሊወሰዱ የሚችሉ በርካታ ማህበራዊና ባህላዊ ልምዶችና እሴቶች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶችንና ህጻናትን ብሎም ማህበረሰቡን የሚጎዱ፤ በተሳሳተ መረዳት የሚተገበሩ ብዙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚፈጸሙባት ሀገር ናት። ከእነዚህም ውስጥ የህጻናት ጋብቻ ስር የሰደደና በሰፊው የሚፈጸም ጎጅ ልማዳዊ ድርጊት ነው። ድርጊቱ የሴት ልጆችን ጤናማ ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል፣ ብሩህ ተስፋቸውን የሚያጨልምና ሰብዓዊ መብትን የሚጥስ ከመሆኑም በላይ ሀገራዊ የዕድገትና የለውጥ እንቅስቃሴዎችን ወደ ኋላ የሚጐትት ነው። ኢትዮጵያ የሕጻናት ጋብቻን በ2017 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ 2025) ለማስቆም ቃል ገብታለች። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የአምስት አመት ሀገራዊ ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም በአማራ ክልል የተዘጋጀ የአምስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ አለ።

የሚፈጸመውን የሕጻናት ጋብቻን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት በሚከናወኑ ተግባራት ዙሪያ ተግዳሮት ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ የሚመለከታቸው ተቋማትና የችግሩ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች (በተለይም ህጻናትና ሴቶች)፤ ስለ አለም አቀፍና ሀገራዊ ህጎች፣ ስምምነቶች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች አጋዥ ማዕቀፎች ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ ነው። በተጨማሪም ማህበረሰቡ በህጻናት ጋብቻ ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማትና አደረጃጀቶቻቸውን በአግባቡ አለማወቅ፤ ችግር ከመፈጠሩ በፊትም ሆነ ከተፈጠረ በኋላ ፤ የችግሩ ተጋላጮችና ተጠቂዎች አስፈለጊውን ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና፤ የጤና አገልግሎቶች እንዳያገኙ እንቅፋት ሆኗል።

ለችግሩ የመፍትሄ አካል ለመሆን በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ዶ/ር ሰብለወንጌል አይናለም እና ዶ/ር ሰዉመሆን ደምሴ፤ እንዲሁም በጀርመን ሀገር የሚኖሩት መምህር ዶ/ር ዞንያ ጆን (Sonja John) በፓርላማ ተወካዮችና ከህዝብ ጋር ባላቸው ግንኙት ዙሪያ ተግባር-ተኮር አነስተኛ የምርምር ፕሮጀክት፤ **The Role of Parliamentarians in Addressing Child Marriage Practices in Amhara, Ethiopia** በሚል ርዕስ ነድፈው እየሰሩ ይገኛሉ። ፕሮጀክቱ የሚደገፈው በእንግሊዝ ሃገር በሚገኝ **PARLIAMENTS AND PEOPLE PROGRAMME** ነው። ስለሆነም ይህን በህጻናት ዙሪያ ያሉ አለምአቀፍ፤ አህጉራዊና፤ ሃገራዊ ፖሊሲዎች፤ ህጎች፤ ስምምነቶችና ስትራቴጂዎች የሚያትት እንዲሁም በህጻናት ጋብቻ ዙሪያ በአማራ ክልል የሚሰሩ ተቋማትና አደረጃጀቶችን የሚጠቁም አጠር ያለ መረጃ ሰጪ ፅሁፍ አዘጋጅተዋል።

የህጻናት ጋብቻን እና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የተመለከቱ ፖሊሲዎች፤ ህጎችና ስትራቴጅዎች

	አለም አቀፍ ህጎች፣ ስምምነቶች፣ ቻርተሮችና ድንጋጌዎች	
1	የተባበሩት መንግስታት ቻርተር (Charter of the United Nations) (እ.ኤ.አ. 1945 ዓ/ም)	ሰብዓዊ መብቶች ዘር፤ጾታን፤ ቋንቋ፤ ሃይማኖትን ሳይለዩ መከበር እንዳለባቸው ይገልጻል
2	ዓለም ዓቀፉ የሰብዓዊ መብት የቃል ኪዳን መግለጫ ሰነድ (እ.ኤ.አ. በ1948 ዓ/ም)	በ30 አንቀፆች ስር የተለያዩ የሰዉ ልጅ መብቶች የሚጣሱባቸዉ ዋናዋና መንገዶችና የሚወገዱበትን ሁኔታ ያመላክታል። ለሰዉ ልጆች እኩልነት፣ አንድነት እና ደህንነትና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል፡
3	ዓለም ዓቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት (እ.ኤ.አበ1976 ዓ/ም)	ለሰዉ ልጆች እኩልነት፣ አንድነት እና ደህንነት በተለይም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል
4	የተባበሩት መንግስታት ስምምነት (እ.ኤ.አ በ1984 ዓ/ም)	ማሰቃየትን እና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸዉ፣ ሰብዓዊነት የጎደላቸዉ እና አዋራጅ የሆኑ አያያዞችን እና ቅጣቶችን ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት
5	የተባበሩት መንግስታት በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛዉንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት (እ.ኤ.አ. በ1979 ዓ/ም)	ሴቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ማግለሎችን እና መድልዎችን ትርጉም አስቀምጦ ይገኛል። አንቀጽ 5 ስር በጾታ እና በስርአተ ጾታ ጉዳዮች ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ሀገራት ማስወገድ እንዳለባቸዉ ይገልጻል።
6	በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የሃይል ጥቃት ተግባራትን ለማስወገድ የወጣ የተባበሩት መንግስታት መግለጫ ስምምነት ሰነድ (እ.ኤ.አ በ1993 ዓ/ም)	በ6 አንቀጽ ስር የተለያዩ የሰዉ ልጅ በተለይም የሴቶች ሰብዓዊ መብቶችን የሚዘረዝር እና እነዚህ መብቶች በሀይል የሚጣሱባቸዉ ዋናዋና እና የሚፈጸሙባቸዉን ሁኔታ ገልጾ ድርጊቶቹ የሚወገዱበትን ሁኔታ ያመላክታል።
7	የሚሊኒየም ዲክላሬሽን ስምምነት/CEDAW/ (እ.ኤ.አ.1987)	በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውንም መድሎዎችን ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት

የህጻናት ጋብቻን እና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የተመለከቱ ፖሊሲዎች፤ ህጎችና ስትራቴጅዎች

	በአህጉር ደረጃ በአፍሪካ የወጡ ስምምነቶች	
1	የዘላቂ ልማት ግቦች እ.ኤ.አ በ2030	ከ 17 ግቦች ውስጥ 3ቱ በሴቶችና ህጻናት ዙሪያ ናቸው ግብ 5 በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚፈጸም ማንኛውም አድሎና መገለል እንዲቆም አላማ ያደረገ ነው ግብ 16 አካታችና ተጠያቂ ተቋማትን በየደረጃው ተደራሽ ማድረግ ግብ 17 የአጋርነትንና ትብብርን ማጠናከር
2	በተባበሩት መንግስታት የምዕተ አመት ዲክለሬሽን (እ.ኤ.አ 2000ዓ.ም ጀምሮ)	ግብ 3 የስርአተ ጾታ እኩልነትን ስለማራመድና ሴቶችን ስለማብቃት ግልጽ የሆነ ድንጋጌ አስቀምጧል
3	የአፍሪካ ሕዝቦች ሰብዓዊ መብት ቻርተር (እ.አ.አ. 1981 ዓ/ም)	ለሰዉ ልጆች እኩልነት፣ አንድነት እና ደህንነት በተለይም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል
4	የአቡጃ ስምምነትና እ.ኤ.አ.በ2003	የሥነ-ተዋልዶ መብትንና ሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን የያዙ ግቦች አሉት መንግስታት ሥርዓተ-ፆታን ያማከለ በቂ ሀብት ለሥነ-ተዋልዶ ጤናና ለታወቁ ገዳይ በሽታዎች መከላከል እንዲመደቡ ጠይቋል።
5	የማፑቶው የድርጊት መርሃ ግብር የአፍሪካ ሀዝቦች እና የሰብዓዊ መብቶች ቻርተር /የባንጁል ቻርተር /(እ.ኤ.አ. በ2006)	የአፍሪካ ሃገራት የፆታዊ ግንኙነትና የሥነ-ተዋልዶ ጤና ማዕቀፍ ሲሆን ከወጣቶች የሥነ-ተዋልዶ ጤናና የሥርዓተ-ፆታ ችግሮችን መፍታትን እንደ አቢይ የትኩረት መስክ አስቀምጧል
6	የአፍሪካ የሕጻናት ደህንነትና መብቶች ቻርተር (እ.አ.አ. በ1990/ በ2001 ዓ/ም)	ለሰዉ ልጆች እኩልነት፣ አንድነት እና ደህንነት በተለይም ለህጻናት ሰብዓዊ መብቶች መከበር ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል።
7	የአፍሪካ የወጣቶች ቻርተር እ.አ.አ. በ2006 በ2009 ዓ/ም	ለወጣቶች ሰብዓዊ መብቶች መከበር ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል

የህጻናት ጋብቻን እና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የተመለከቱ ፖሊሲዎች፤ ህጎችና ስትራቴጅዎች

	በኢትዮጵያ የተዘጋጁ ፖሊሲዎች፤ ህጎችና፤ ስትራቴጂዎች	
1	የብሔራዊ ሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ (እ.ኤ.አ 1986 ዓ.ም)	ሴቶች ያለዕድሜያቸው ባል እንዳያገቡ እንዲሁም የጠለፋና የግዳጅ ጋብቻ ውስጥ እንዳይገቡ ያበረታታል። የሴቶች ግርዛትና ሌሎች ከውሊድ ጋር ተያይዘው የሚከናወኑ ልምዶች በሴቶች ላይ የሚያደርሱት ጐጂ ተፅዕኖ ላይ ትኩረት ያደርጋል። የሴቶች የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ላይ ትኩረት ያደርጋል
2	ብሔራዊ የሕጻናት ፖሊሲ (እ.ኤ.አ 2009 ዓ.ም)	የህጻናት ጋብቻን፤ የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶችን፤ የህፃናት ጥቃት፣ ሕገ-ወጥ ዝዉዉር፣ የጉልበት ብዝበዛና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤እና ጥቃት የደረሰባቸዉ ህፃናት ተገቢዉን የተሀድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ ተስማሚ ችሎቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር ላይ ትኩረት ያደርጋል።
3	ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ (1985 ዓ.ም)	የህዝብ ቁጥር መጠንን ከኢኮኖሚው እድገት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ያበረታታል።ይህም የእናቶችን ሞት ከመቀነስ አኳያና ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና የፖለቲካ ሁኔታ ያሻሽላል።
4	የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ (እ.ኤ.አ 1986 ዓ.ም/)	የሴቶች ትምህርትን ያለእድሜ ጋብቻንና ወሊድን እንደሚቀንስ፣የቤተሰብ ምጣኔ አጠቃቀምን እንደሚያሳድግ፣ከትዳር አጋር ጋር ያለውን ተግባቦት እንደሚያሻሽልና የሴቶችን ማህበራዊ ደረጃ እንደሚያሳድግ በግልጽ አስቀምጦታል።
5	የጤና ፖሊሲ /እ.ኤ.አ 1985 ዓ.ም/፣	ለሥነ-ተዋልዶ ጤና ማለትም ለእናቶችና ለህፃናት ጤና ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። የሥነ-ተዋልዶ ጤና ስልት፣የወጣቶች የሥነ-ተዋልዶ ጤና ስልት(እ.ኤ.አ 2006-2015) እንዲነደፉና በሌሎች መመሪያዎችና ፓኬጆች እንዲታገዙ አድርጓል።
6	ግብርና መር የኢንዱስትሪ ስትራቴጂ /እ.ኤ.አ 1993 ዓ.ም/፣2000 ተሻሽሏል	የምግብና ዋስትና ማሻሻል፣ለግብርና ምርቶች ተገቢውን የገበያ እድል መፍጠር፣አርሶአደሮችን ከውጭው ገበያ ጋር ማገናኘትና የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ላይ ትኩረት ያደርጋል
7	የባህል ፖሊሲ /እ.ኤ.አ 1989 ዓ.ም/፣	በተለያሉ ብሔረሰቦችና ባህሎች ውስጥ የሚገኙና ለጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና አስተሳሰቦች ጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና ጥበቃ ልዩ ክትትል እንደሚደረግ ይገልጻል። በህፃናት አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ዕድገት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶች አንዲወገዱ አቅጣጫዎች አስቀምጧል።
8	የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ፖሊሲ /እ.ኤ.አ 1989 ዓ.ም/	አደገኛ የሆኑ ንጥረ ነገሮችና ከአየር ብክለት ጋር በተያያዘ ሕፃናትና ሴቶች በቤት ውስጥ ረጅም ሰዓት በመቆየት የተለያዩ ሥራዎችን ስለሚሠሩ በተቃጠለ ጢስ የመበከል ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ ነው።

የህጻናት ጋብቻን እና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የተመለከቱ ፖሊሲዎች፤ ህጎችና ስትራቴጅዎች

	በኢትዮጵያ የተዘጋጁ ፖሊሲዎች፤ ህጎችና፤ ስትራቴጂዎች	
9	የእድገትና ማህበራዊ ዋስትና ፖሊሲ (እ.ኤ.አ 1996 ዓ.ም)	ለሥርዓተ-ፆታ ልዩ ትኩረት በመስጠት በተለያዩ ቦታዎች (የሥራቦታዎችን ጨምሮ) በሴቶች ላይ የሚፈፀመው አድሎ እንዲቆምና የጤና አገልግሎቶች አቅርቦት እንዲሟላ በማድረግ ላይ ያተኩራል፡፡በተጨማሪም ፖሊሲው የሴቶች ገቢ አነስተኛ እንዲሆን ምክንያት የሆኑ ችግሮችን በመፍታትና የሥራጫናን መቀነስን ያራምዳል፡፡
10	የኢፌዴሪ የወንጀል ፖሊሲ (እ.ኤ.አ 2003 ዓ/ም)	የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ፖሊሲ አቅጣጫዎች መካከል የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ የህዝብን፣ የግለሰቦችንና የሀገርን ሰላምና ደህንነትን ማስጠበቅ ቀዳሚ አጀንዳ መሆኑን ይገልጻል፡፡
11	የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ (እ.ኤ.አ 2012)	በተለያዩ መንስኤዎች ምክንያት ለችግር ተጋለጭ ለሆኑ ሴቶችና ህጻናት ማህበራዊ ከለላ፤ ጥበቃና፤ አገልግሎቶች የሚያገኙባቸውን የተለያዩ ስልቶች ነድፎ አስቀምጧል

	በኢትዮጵያ የወጡ የህግ ማዕቀፎችና ሌሎች የሰነድ ማዕቀፎች	
1	የፌዴራሉና የክልሉ ሕገ መንግስት	አንቀጽ 25፣ 34፣ 35 እና 89/7 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በሁሉም የህይወት መስኮች ሴቶች ከወንዶች እኩል መሆናቸውን ያረጋገጣሉ በንኡስ አንቀጽ (35.8) ላይ የቤተሰብ እቅድ መረጃን የማግኘት፤የወሊድ ፈቃድ እንዲያገኙ (35.5)፤ሴቶችን የሚጨቁኑና በአካላቸውና በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ልማዳዊ ድርጊቶች የመጠበቅ (35.6) መብት
2	የተሻሻለዉ የፌዴራሉና የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕጎች፡- (1992ዓ.ም)	የጋብቻ እድሜ ለሴቶችና ለወንዶች እኩል 18 አመት መሆን እንዳለበት ደንግጓል፡፡ ጋብቻውም በሁለታቸው ስምምነት የሚፈፀም መሆን እንዳለበት ፍቺውም በዚሁ አግባብ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ሀጉ ሁለቱንም ፆታዎች በእኩልነት ቤተሰብ መምራትና ንብረት የማስተዳደር መብት አጎናጽፏቸዋል፡፡
3	የኢፌዲሪ ወንጀል ሕግ (1949 ዓ.ም) የፍትሃ ብሔር ሕግ (1952 ዓ.ም)	-በሴቶች ላይ የሚፈፀም ማንኛውንም ጥቃት ማለትም ፆታዊና የቤት ውስጥ ድብደባ፣ ህገ ወጥ የሰወች ዝውውር፣ ጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ግርዛትና ጉልበት ብዝበዛ፣ በወንጀልነት ፈርጆ ይደነግጋቸዋል -በመደፈርና ለአካለ መጠን ባልደረሱ ሴቶች የተፈጠረን ጽንስ ማቋረጥን ይፈቅዳል -ሴተ ልጅ ላይ ግርዛት በሚፈጽሙ ገራዥች ላይ ቢያንስ የሦስት ወር እስራት፣ ወይም የ500 የኢትዮጵያ ብር የገንዘብ መቀጮ ይጥላል፡፡ እጅግ አደገኛ በሆነ ሁኔታ ግርዛት የሚያከናውኑትን ደግሞ ከአምስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል -ለአቅመ አዳም/ሄዋን ካልደረሰ/ች ህፃን ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም ከ3 እስከ 15 ዓመት የሚደርስ ቅጣት እንደሚያስከትል በሕግ ተደንግጓል -ለአቅመ አዳም/ሔዋን ባልደረሱ ሕፃናት ላይ አስጸያፊ ወሲባዊ ደርጊት ሲፈፀም የሚያሳዩ ምስሎችን ያሰራጨ ሰው በአንድ ዓመት እስራትና በ10,000 ብር (500 የአሜሪካን ዶላር) የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል፡፡ -ትርፍ ለማግኘት ሲባል ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ሕፃናትን ለወሲብ ድርጊት ማሰማራትና የወሲብ ንግድ እንዲጀምሩ መገፋፋትን ይከለክላል፡፡

	በኢትዮጵያ የወጡ የህግ ማዕቀፎችና ሌሎች የሰነድ ማዕቀፎች	
4	የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የመንግስት ሰራተኞች መተዳደሪያ አዋጅ ቁጥር 515/2007 የአማራ ክልል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2003 አም	የሴቶችን መብት በመደገፍ በቅጥር፣ በምደባ፣ በዝውውር፣ በስልጠናና በደረጃ እድገት ወቅት ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ እንዲሁም ከጥቃት የነፃ-የሥራ አካባቢን በመፍጠር አዎንታዊ የድጋፍ ማእቀፍ እንዲተገበር ደንግጓል
5	የብሔራዊ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት መከላከልና ምላሽ መስጫ ስትራቴጂ ሰነድ	የሴት ልጅ ግርዛትና የልጅነት ጋብቻና ሌሎችን ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት ሶስት ስትራቴጅያዊ ምሰሶዎችን ማለትም መከላከል፣ ጥበቃ ማድረግና ወሳኝ አገልግሎቶችን ማሟላት የሚሉትን አስቀምጧል
6	የፌደራሉና የአማራ ክልል 2ኛዉ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ	በስትራቴጅዉ ዉስጥ የህጻናት ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶችን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ጉዳዮች ጭምር ተካትተዉ ይገኙበታል
7	የብሄራዊ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር	የሴቶችን እና የህጻናትን የሀይል ጥቃት ድርጊቶችን በግልጽ የሚያወግዙ የተለያዩ መልእክቶችን አካትቶ ይዟል ሰነዱ ተግባራት ሊፈጸሙ የሚችሉባቸዉን ሁኔታዎች፣ የፈጻሚዎችን ማንነት፣ ተግባራት የሚፈጸሙበትን ጊዜ፣ የድጋፍ፣ የክትትል፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ጉዳዮች አካትቷል
8	የኢትዮጵያ የሴቶች የልማት፣ የእድገትና የለዉጥ ፓኬጅ እና ስትራቴጂ፡-	ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሙሉ በሙሉ ነፃ የሆኑ አካባቢዎች በመፍጠር በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጌጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ፡- ስር ነቀል የህብረተሰብ ንቅናቄ መፍጠር፣ የጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ፈፃሚዎችን በመለየት በየአካባቢያቸው ተከታታይ የሆነ ትምህርት መስጠት፣ ፈጻሚዎች የገቢ ማስገኛ ስራዎች ማሰማራት፤ በማይታረሙት ላይ ህጋዊ የቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ በትምህርት ቤቶች ግንዛቤ ማስጨበጥ እና በሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንዲካተት ማድረግ፣ግብረ ሃይሎችን በየደረጃው ማቋቋምና የተቋቋሙትን ማጠናከር፣
9	የህጻናት ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም የተዘጋጀ ፍኖተ ካርታ (እ.ኤ.አ 2020–2024)	የህጻናት ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት መንሰኤዎችን፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት እና አሁን ያለበትን ደረጃ ይዘረዝራል ችግሮቹን እ.ኤ.አ በ2025 ከኢትዮጵያ ለማስወገድ አምስት የተግባር ምሰሶዎችን አስቀምጧል፡-የልጃገረዶችን እና ቤተሰቦቻቸውን አቅም ማጎልበት፤ማህበረሰቡን ማሳተፍ፤የአገልግሎቶችን አሰጠጣጥ፤ ተደራሽነትና፤ ቀለጣፋነት ማሳለጥ፤ምቹ አካባቢን መፍጠር እና ማጠናከር፤የመረጃዎችን አያያዝና አጠቃቀም መጨመር
10	በአማራ ክለል የህጻናት ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ስትራቴጂካዊ ሰነድ	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዉስጥ እየተፈጸሙ ያሉትን የህጻናት ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት መከናወን ያለባቸውን ዝርዝር ተግባራትና ባለድርሻ አካላት ሚና አስቀምጧል

የህጻናት ጋብቻን ለመከላከል/ለማስቆም የሚሰሩ ተቋማዊ አደረጃጀቶች

1. የአብክመ ሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ተግባር እና ኃላፊነት

- የህፃናት ጋብቻ ወንጀል ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት የተዘረጋዉን አሰራር ያስተባብራል፣ ይደግፋል ይከታተላል።

- ለልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስልጠና ይሰጣል፤ የስነ-ልቦና ድጋፍና የምክር አገልግሎት መስጠት፤ ለህፃናት እንክብካቤ የሚሠጡ ተቋማትን ያፈላልጋል፤ በህፃናት ጋብቻ እና በሴት ልጅ ግርዛት ወንጀል ሰለባ ለሆኑ ህፃናት ማቆያ የሚሆን ምግብ እና መጠለያ ያመቻቻል፤ መልሰው የሚቋቋሙበትን መንገድ ያመቻቻል።

- በህፃናት መብቶች በተለይ የህፃናት ጋብቻ መንስዔ እና ውጤቱ ላይ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ በጥናቱ ለተገኙ ችግሮች ለሚመለከተው አካል የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል።

- ህፃናትን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ህጎች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎችን በመመርመር ያለባቸውን ክፍተት በመለየት የሚስተካከሉበትን መንገድ ለህግና ፖሊሲ አውጭዎች ይጠቁማል።

2. የአብክመ ፖሊስ ኮሚሽን፤ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ መ/ቤት እና ፍርድ ቤት ተግባር እና ኃላፊነት

- የመብት ጥሰት ላጋጠማቸው ህፃናት ነፃ የህግ ምክና ከለላ መስጠት፤ በፍርድ ቤት መከራከር ፤በምርመራ ሒደት የተጎጂዎችን አቆያየትና አያያዝ መከታተል ፤ በእርቅ እና በድርድር የሚያልቁ ጉዳዮችን ማማከር ።

- የህፃናት ጋብቻ ጉዳዮች ምቹ በሆነ ችሎት ቅድሚያ በመስጠት እንዲታይ ማድረግ።

- የተጎጂዎችን ሚስጥርና ነፃነት ለመጠበቅ ከተቻለ በሲሲቲቪ ካሜራ እና በማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ በመታገዝ እንዲታይ ማድረግ፤ የሲሲቲቪ ካሜራ በሌላቸው ቦታዎች ደግሞ በተቻለ መጠን በዝግ ችሎት እንዲታይ ማድረግ።

- ተጠርጣሪን በህግ መሰረት መያዝ፤ ማቆየት፣ እንዲሁም በ48 ሰዓት ፍርድ ቤት ማቅረብ ፤ ምርመራን ማጠናቀቅ፡፡

- የምስክሮችን ቃል ትኩረት ሰጥቶ በፍጥነት መቀበል፣ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ለተጎጂዎችና ለምስክሮች አስፈላጊውን ጥበቃ ማድረግ፡፡

- የህፃናት ጋብቻ ወንጀል ሰለባ የሆኑ ህፃናት ተገቢውን የህግ፣ የህክምና፣ የስነ-ልቦና እና ሌሎችን ድጋፎች እንዲያገኙና ወደማህበረሠቡ እንዲቀላቀሉ የሚያስችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

- የህፃናት ጋብቻ ወንጀልን በተመለከተ ለማህበረሰቡ እና ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ ማሳደጊያ የንቃተ-ህግ ትምህርና ስልጠና መስጠት፡፡

- ህፃናትን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ህጎችን በመመርመር ያለባቸውን ክፍተት በመለየት የሚስተካከሉበትን መንገድ ለህግና ፖሊሲ አውጭዎች ይጠቁማል፡፡

3. የአብክመ ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተግባር እና ኃላፊነት

- ፕሮጀክት ቀርፆ ሀብት በማፈላለግ የመጠለያ እና የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕከላት እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡

- የህፃናት ጋብቻ ወንጀል ሰለባ ለሆኑ ህፃናት የሚሆን ምግብ እና መጠለያ ያመቻቻል፤ የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤ቤተሰብ ለሌላቸው ወንጀል ሰለባዎች አማራጭ የቤተሰብ አገልግሎት የሚሠጡ ተቋማትን ያፈላልጋል፡፡

- የህፃናት ጋብቻ ወንጀል ሰለባ ለሆኑ ህፃናት ተገቢውን የህግ፣ የህክምና፣ የስነ-ልቦና እና ሌሎችን ድጋፎች እንዲያገኙ ወደሚመለከተው አካል የቅብብሎሽ አሰራር ይልካል፡፡

- የህፃናት ጋብቻ በተመለከተለልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ትምህርት፣ እንደአስፈላጊነቱ ስልጠና ይሰጣል፡፡

4. የአብክመ ጤና ቢሮ ተግባር እና ኃላፊነት

- የህፃናት ጋብቻን በተመለከተ ለእድሜ ምርመራ እና ለተለያዩ ምርመራዎች ወደ ህክምና ተቋማት ለሚላኩ ህፃናት የሚሰጡ የህክምና አገልግሎቶች፣ ከሌሎች ታካሚዎች በተለየ ሁኔታ ቅድሚያ እንዲያገኙ በማድረግ፤ ጥራታቸውን የጠበቁ የማስረጃዎች ትርጉም ከክፍያ ነፃ፣ ወቅቱን የጠበቀ እና ተሟልተው ለፖሊስ ወይም ለጠየቀው የፍትህ አካል በነፃ መሰጠታቸውን ይከታተላል።

- ለህፃናት የህክምና ምርመራ የሚሠጡ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ይመድባል፤ ለአገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶችን ያሟላል።

- ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና ማንኛውም ጥቃት በጤና ላይ ያለውን ጉዳት ለህብረተሰቡ ያስተምራል።

- የህክምና ባለሙያዎች አስፈላጊ ሲሆንና በተጠየቀ ጊዜ የሙያ ምስክርነት ይሰጣል።

5. የአብክመ ትምህርት ቢሮ ተግባር እና ኃላፊነት

- የህፃናት ጋብቻ የሚያደርሰውን ጉዳት በየትምህርት ቤቶች በተለያዩ መንገዶች እንዲተላለፉ ያደርጋል።

- የህፃናት ጋብቻ ወንጀል ሰለባ ለሆኑ ህፃናት ተገቢውን የህግ፣ የህክምና፣ የስነ-ልቦና እና ሌሎችን ድጋፎች እንዲያገኙ ወደሚመለከተው አካል የቅብብሎሽ አሰራር ቅጾችን በመጠቀም ይልካል።

- የህፃናት ጋብቻ የተፈፀመባቸው ተማሪዎች በደረሠባቸው ወንጀል ምክንያት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የሚቻልበትን መንገድ ይሰራል።

- ተማሪዎችን በክበባት እንዲደራጁ እና ስለህፃናት ጋብቻ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ሊፈጸም ሲል እና ሲፈፀም ጥቆማ እንዲያደርጉ ትምህርት ይሰጣል።

- ለወላጆች፣ ለህፃናት ጋብቻ ወንጀል ሰለባዎች፣ ለልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ትምህርት፣ እንደአስፈላጊነቱ ስልጠና ይሰጣል።

6. የአብክመ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ተግባር እና ኃላፊነት

- የህፃናት ጋብቻን ለማስቀረት የሚያስችሉ ባህሎችን ያበለጽጋል፡፡
- በህፃናት መብቶች በተለይ የህፃናት ጋብቻ መንስዔ እና ውጤቱ ላይ የተለያዩ የኪነ ጥብ ስራዎችን በማሰራት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፡፡

7. የጎጂ ልማዳዊ ድርጊት አስወጋጅ ጥምረት

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በተለይም የህጻናት ጋብቻ በሴቶችና ህጻናት ላይ እያደረሱ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ከተናጠል ጥረት ባለፈ በተቀናጀ አካሄድ ለመስራትና የተሻለ ውጤት ለማምጣት በማሰብ የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ቢሮ አስተባባሪነት ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ የጎጂ ልማዳዊ ድርጊት አስወጋጅ ጥምረት እንዲመሰረት ተደርጓል፡፡ ጥምረቱ ሁለት አይነት ኮሚቴዎች አሉት፡-

1ኛ፡- **የቴክኒክ ኮሚቴ** ሲሆን በየሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት የሚመራ ሆኖ የተዋቀረዉም የወረዳ/ቀበሌ የሴክተር መስሪያ ቤቶች ጽ/ቤቶች የስርዓተ ጾታ ባለሙያዎች ወይም ተጠሪ የሆኑ አካላት፤ የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ወዘተ...በማካተት ነዉ፡፡

2ኛ፡- **አስተባባሪ/መሪ ኮሚቴ** የወረዳ የሴክተር መስሪያ ቤቶች ጽ/ቤቶች ሃላፊነት ላይ ያሉ አካላት ስብስብ ሆኑ በወረዳ/ቀበሌ መስተዳድር/አስተዳዳሪ የሚመራ ቡድን ነዉ፡፡

በመሆኑም በእነዚህ አደረጃጀቶች አማካኝነት ማህበረሰቡ የህጻናት ጋብቻ ጉዳይን ለመከላከልና ለማስቆም የተለያዩ መረጃዎችን፤ ግንዛቤዎችን ለማግኘትና ችግሮች ሲፈጠሩ ወደመፍትሄ አካል ለመሄድ መጠቀም ይችላል፡፡

8. መንግስታዊ ያልሆኑ አደረጃጀቶች

በተጨማሪም መያድ (መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) እና ማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀት ተጠሪዎች እንደየአካባቢዉ ተጨባጭ ሁኔታ ይኖራሉ፡፡ በዚህ አደረጃጀት በፕሮጀክት ደረጃ በሴቶችና ህጻናት ችግሮች ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን ከሴክተር ቢሮዎች ጋር በመሆኑ በእነሱ በኩል አገልግሎቱን ማግኘት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ቦታዎች SAFE HOUSE (መቆያ ቦታዎች) አሉ እነርሱንም ማማከር ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ሲቪክ ማህበራት፤ የሃይማኖት ተቋማት፤ እንዲሁም ማህበራዊ አደረጃጀቶችና ግለሰቦች ጉዳዩን ወደሚመለከታቸዉ አካላት ለማድረስ አጋዥ የሆኑ አካላት ናቸዉ፡፡

በቀበሌ ደረጃ የሚሰሩ ተቋማዊ አደረጃጀቶች

ተቋም	ምን አይነት አገልግሎት ይሰጣል?	ማንን ማግኘት ይቻላል?
መስተዳድር ጽ/ቤት	መረጃ ለማግኘት ሪፖርት ለማድረግ	አስተዳዳሪዉን
		የስርዓተ ጾታ ተጠሪ/ባለሙያ
ሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት	መረጃ ለማግኘት ሪፖርት ለማድረግ ጉዳይ ለማስፈጸም	የሴቶች አደረጃጀት ቡድን መሪ
		የህጻናት ጉዳይ ቡድን መሪ
ትምህርት ቤት	ግንዛቤ ለማግኘት	የት/ት/ቤቱ ዳሬክተር
	መረጃ ለማግኘት	የት/ት ቤቱ መምህራን
	ሪፖርት ለማድረግ	የሴቶች ክለብ/ሌሎች ክለቦች
		የህጻናት ፓርላማ
		የስርዓተ ጾታ ተጠሪ
ፖሊስ	ሪፖርት ለማድረግ	የአካባቢ ፖሊስ/አቃቢ ህግ
	ግንዛቤ ለመያዝ	የስርዓተ ጾታ ተጠሪ/ባለሙያ
በማህበረሰብ ደረጃ ከማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀቶች	መረጃ ለማግኘት ግንዛቤ ለማግኘት ሪፖርት ለማድረግ	የሴቶች ተወካይ
		የሴቶች የልማት ቡድን ተጠሪ
		የሴቶች 1 ለ 5 ቡድን ተጠሪ
		የሴቶች ሊግ መሪ
		የወጣቶች ሊግ መሪ
		የአካባቢ ሽማግሌዎች
		ዕድር፣ ጎረቤት፣ ጓደኛ፣ ዘመድ
ጤና	መረጃ/ግንዛቤ/ሪፖርት	ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች
በሃይማኖት ተቋማት ቤተ እምነቶች		የሀይማኖት መሪዎች
		የነፍስ አባቶች
		የአካባቢ ተዋቂ ሽማግሌዎች

GLOBAL RESEARCH NETWORK ON PARLIAMENTS AND PEOPLE

This project is funded by PARLIAMENTS AND PEOPLE PROGRAMME

በ2010 ዓ.ም በፋርጣ ወረዳ፤ አማራ ክልል ሊያገቡ ሲሉ የተገኙ ህጻናት

GLOBAL RESEARCH
NETWORK ON
PARLIAMENTS
AND PEOPLE

This project is funded by
PARLIAMENTS AND PEOPLE PROGRAMME

የፕሮጀክቱ መለያ ኮድ፡ PPs 190505

https://www.facebook.com/GRNPP/
@GRNPP1

Graphics Design Linknet
0918 76 50 51
ባህር ዳር